# ሶስት ጊዜ አቅማምተው የገዙት....

ቅዳሜ መጋቢት 17 2003 ዓ.ም.11:00 ሰዓት መርካቶ ገበያ ደርቷል፡፡ ወ/ሮ ጤናዬም የቤት አስቤዛቸውን ለመግዛት ከእህተቸው ጋር ወደ መርካቶ አቅንተዋል፡፡

መጋቢት 23 ደግሞ በዕጣ ለደረሳቸው ኮንዶሚኒየም ክፍያ የሚሆን ብር ያስፈልጋቸዋል፡፡ ይህ ቀን ደግሞ የመጨረሻው ቀን ነው፡፡ ብዙ ቦታ ሄደው ቢጠይቁም ለችግራቸው የሚደርስ አንድም ሰው አልተግኘም፡፡

ባለቤታቸው 400 ብር እየተከፈላቸው የጥበቃ ስራ ያከናውናሉ፡፡ ስድስት ልጆችም አፍርተዋል፡፡ በዛ ቀን የቤት አስቤዛቻውን ገዝተው ወደ ቤት ለመመለስ የመርካቶ ቆይታቸውን እያጠናቀቁ ነው፡፡



ቆም አሉ፡፡ ልግዛ እንዴ ሲሉ ጠየቁ፡፡ አይ ይቅርብኝ በማለት መንገዳቸውን ቀጠሉ፡፡ ትንሽ እንደሄዱ አሁንም ቆም አሉ፡፡ ምን ይሻለኛል ልግዛ ወይስ ይቅርብኝ አመነቱ፣ መግዛቱን ትተው መንግዳቸውን ቀጠሉ፡፡ አብረዋቸው የሚሄዱት በእህተቸው ሁኔታ ግራ ተጋብተዋል፡፡ምን ሆና ነው እያሉ ለራሳቸው መጠየቃቸው አልቀረም፣ ደፍረው ግን አልጠየቁቸውም፡፡

ለሶስተኛ ጊዜ ወደ ኋለ ቀረት አሉ፡፡ አሁን መወላወል የለም፣ ወሰኑ፡፡ ገዙ፡፡ እህተቸውም ምንሆነሽነው ወደ ኋላ ቀረት ቀረት የምትዪው ሲሏቸው አይ ምን አልሆንኩም ሲሉ ይምልሳሉ፡፡

እሁድ መጋቢት 18 የገዙትን ሎተሪ ከማውጫው ጋር አስተያዩት፡፡ በአዲስ ከተማ ክፍለከተማ ነዋሪ የሆኑት የ45 ዓመቷ ወ/ሮ ጤናዬ ሶስት ጊዜ አቅማምተው የገዙት መደበኛ ሎተሪ 75,000 ብር ዕድለኛ አድረጓቸዋል፡፡ ደስታቸው ወደር የለውም፡፡ በገንዘብ

ችግር ሊያመልጣቸው የነበረውን የኮንዶሚኒየም ቤት አሁን ከሳቸው እጅ አላፈተለከም፡፡

ዕድሜ ለዕድል

“አሁን በደረሰኝ ብር በግማሹ የኮንዶሚኒየም ክፍያዬን እከፍላለሁ፡፡ በቀሪው ብር ደግሞ ህይወቴን የሚለውጥ ስራ እሰራለሁ፡፡ በኮንዶሚኒየሙም ደስታየን አገኛለሁ” ብለዋል በደረሳቸው ብር ምን ለማድረግ እንዳቀዱ ተጠይቀው፡፡